# በዴሞክራሲ ሽፋን ሀገርን ማጥፋት አይቻልም!

ደሞክራሲ አለገደብ ብሎ በመታገሉ የሚታወቀው ኢሕአፓ ነው። ወታደራዊው አገዛዝ በሰ በብ አስባቡ የሕዝብን መብት ሊገድብ ሲነሳ ዴሞክራሲ አለገደብ ብሎ የታገለው ኢሕአፓ ብቻ ነው። የሕዝብ መሰረታዊ መብቶች መገደብ፣ መታፈን መቀነስ የለባቸውም በሚል ኢሕአፓ ትግል አካሂዷል። ዛሬ በሕዝብ መብት ሽፋን ሀገር አጥፊ ሰበካ ሲሰራጭ ኢሕአፓ ይህን በዝምታ ሊያልፈው አይችልም።

የሕዝብ ዴሞክራሲያዊ መብት ገደብ የለውም ማለት በዚሁ ተመስርቶ ሀገርን አፍራሽ እንቅ ስቃሴ ማካሄድ መብት ነው ማለት አይደለም። ከሁሉም በፊትና በላይ ዋናው የሀገር ህልውና ነው። ይህንን አፍርስ አጥፉ የሚል ዴሞክራሲያዊ መብት ሊኖር ሆነ ሊፈቀድ አይችልም። ከመሰረታዊ የሀገር ህልውና አንፃር መብት ሊገደብ መቻሉንም ማወቅ ያስፈልጋል ማለት ነው። አምባገነኖች በልምድ የሀገር ደህንነት በሚል ሽፋን የሕዝብን መብት ነጋ ጠባ ማገድ ና ማፈን ይቀናቸዋል። የሀገር ደህንነት ምን መሆኑን ግን ሕዝብ ሳይሆን ራሳቸው ናቸውና ወሳኝ ለሀገር ተቆርቋሪ ነን ባዮቹ አረመኔዎች የሕዝብን የመብት ጥያቄ ህገወጥ ለማድረግ ሁሌም ሲፍጨረጨሩ ያየነው ነው። መብት ፍፁም ነው--መገደብም የለበትም። ግና ደግሞ መብት በሚል ሽፋን በንዝህላልነት ሀገርን ማጥፋት አይቻልም። ዛሬ የዴሞክራሲ መብት በሚል ሽፋን ሀገርን ለግንጠላ እያመቻቹ ያሉ ክፍሎች ይህንን መሰረታዊ ሀቅ መረዳት ይገባቸዋል።

በአሁኑ ጊዜ ሀገራችን የባዕዳንና የገንጣዮች ሴራና ጥቃት እየደረሰባት ነው ። መለስ መውደ ቁ አይቀርምና መለስን በሌላ ወያኔ ለመተካት ዝግጅቶች አሉ። ለዚህም ሀገር አጥፊ ሽግግር አጃቢዎች ተዘጋጅተዋል። ይህን ሴራ ግን ኢሕአፓ እያጋለጠ ነውና በጠላትነት ተመድቦ እየተቀጠቀጠ ነው። ሂደቱ ሁሉ ግን ከዴሞክ.ራሲ ጋር ቅንጣትም ግንኙነት ያለው አይደለ ም። ዴሞክራሲ በሁሉም አፍ የገባ ቃል ቢሆንም ቅሉ በዴሞክራሲ ስም ሀገርን አጥፊ መስመር ሊገፋ አይችልም። በአሁኑ ወቅት በመብት ሽፋን ሀገርን መገንጠል ተገቢ ነው፣ የዴሞክራሲ መብት ነው በሚልም እየቀረበ ነው። የመገንጠል መብትን ተግባራዊነት እናስከ ብር የሚሉ አወቅን ባይ  የገበያ ምሁራንም ብቅ ብለዋል።  ይህን ርኩስ ዓላማ ለመግፋት ደግሞ ሕዝበ ውሳኔ ይደረግ የሚለውን ቀኖና እያሰሙ ናቸው። ሕዝበ ውሳኔ ወይም ፌፌሬን ደም የተባለው ነጋ ጠባ ባልሆነ ሁኔታ ሁሉ የሚካሄድ አይደለም። የኤርትራውን አይተናል። ነፃነት ወይስ ባርነት በሚል በአጣብቂኝ የገባ ሕዝብ ምርጫ ተነፍጎ ድምፀ ስጥ የተባለበት ነው። ውሳኔውን ተቆጣጣሪም ሆነ ቆጣሪ ያው ሻዕቢያ ነበር። ቀልድ፣ቧልት። የዘመኑ ጅሎች ደግሞ  የኦነግና የኦብነግን የለየለት የግንጠላ መርሀ ግብር በስራ ለማዋል ሲሉ ለሕዝቦቹ

ሬፈሬንደም መብት ይሰጥ፤ ህዝበ ውሳኔ ያድርጉ ይላሉ፡፡ ይህን በተመለከተ ደግሞ ከኢትዮጵ ያ ቅኝ አገዛዝ ነፃ ለመሆን እየታገልኩ ነኝ የሚለው ኦነግ ለምሳሌ ህዝበ ውሳኔው የሚመለከተ ው ኦሮሞዎችን ብቻ ሲሆን አማራጩም በኢትዮጵያ ጭቆና መቀጠል ወይስ ነፃ ኦሮሚያን መመስረት የሚል ይሆናል ሲል ዕቅጩን አስቀምጧል፡፡ ማነው ኦሮሞ? ማነው ኦሮሞ ያልሆ ነው? ይህን ወሳኝ ኦነግ እኔ ነኝ ባይ ነው፡፡ ኢትዮጵያዊ ነኝ ባዩን ኦሮሞ ኦነግ ቦታ የሚሰጠው አይመስልም፡፡ ይህንን እየደገፉ ያሉ ምሁራን ተብዬዎች ለትዝብት ተዳርገዋል፡፡

ዴሞክራሲ የሕዝብና የሀገርን ጥቅም ማስጠበቂያ እንጂ ሀገርን ህዝብን ጎጂና አጥፊ ሊሆን የሚችል አይደለም፡፡ ለዴሞክራሲ የምንሰጠው ትርጉም ሀገርና ሕዝብን መሰረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡ አለገደብ ስንል ከዚህ አንፃር እንጂ ሀገርን የማተራመስና ህልውናዋን የማጥ ፋት መብትን በሚመለከት ገደብ የለም ነፃ ናቸው ለማለት ሊሆን አይችልም፡፡ ኢትዮጵያን እንገነጣጥል ለሚሉ መድረክና መብት መስጠቱ ዴሞክራሲያዊነት አይደለም--ንዝህላልነት እንጂ፡፡ የሀገር ህልውናን በተመለከተ የሆነው ሁሉ ምን አለበት፤ ለምን አይሞከርም ወዘተ በሚል ሀላፊነት በጎደለው መንገድ መለፍለፉና መጮሁ በአጥፊነት የሚያስፈርጅ ነው፡፡ በሀገ ረ ደረጃ ዴሞክራሲያዊ ሁኔታ ሰፍኖ የሚካሄድ ህዝበ ወሳኔና በጭቆና ማጥ ውስጥ ሕዝብ

እየተሳቀየ የሚካሄድ ውሳኔ አንድ አይደለም፡፡ አማራጩ የሚቀርብበት ሁኔታም ከሀገር ህል ውና አንፃር ጠቀሚ መሆን ይገባዋል፡፡ ነፃነት ወይስ ባርነት ቧልት አማራጭ ነው፡፡ ማን ባርነ ትን ሊመርጥ? በዚህም መሰረት የኦሮሞን ህዝብ ለኦነግ አሳልፎ ሰጥቶ በል በኦነግ ቁጥጥር ስ ር ነፃ ኦሮሚያንወይስ ጨቋኝ ኢትዮጵያን የትኛውን ትመርጣለህ ብሎ ማቅረቡ የጅሎች ጨ ዋታ ነው፡፡ ጨቋኞች የብልህ ፖለቲካ በሚል ያለው ተጨባጭ ሁኔታ ይህ ነው የሚሉት በሀ ቅ ሲመረመር ተጨባጭ ሁኔታ አይደለም፡፡ የኢትዮጵያን የነገ ዕጣ በዘረኝነትና በክልል የምን ወስነው ሊሆን አይችልም፡፡ ክልልና አንቀፅ 39 የወያኔ ተጨባጭ ሁኔታ ናቸው--የኢትዮጵያ አይደሉም፡፡ የሚሰረዙ የሚደለዙ የሚወገዱ ናቸው፡፡

ዴሞክራሲ ስንል የሕዝብና የሀገርን ጠቅም በማስቀደም የሀገርን ህልወናና የሕዝብን መብት ለማስጠበቅ እንጂ በሀገር ህልውናና ላይ ለመጫወት አይደለም፡፡ የሽግግር መንግስት ጉባዔና ሂደትም የተራ ቅርጫ ዓይነት ሁሉም ድርሻውን ሙዳ ስጋ /ክልል ይዞ የሚገነጠልበትን ሁኔታ ማዘጋጂያ አይደለም፡፡ የሀገር ህልውና ጉዳይ በቀላሉ የሚታይና ሀላፊነት በጎደላቸው ምሁር ተብዬዎች ተራ ውሳኔ የሚደመደም አይደለም፡፡ ለዘመናት ደም የፈሰሰላትን ኢትዮ ጵያ ዛሬ የተወሰኑ ከሀዲና አሳፋሪ ምሁራን ተብዬዎች በባዕድ ሀገር ሆነው ትፍረስ ትገንጠ ል ብለው ስለጮሁ ብቻ ሀገር ለፍርሻ ልትዳረግ አትችልም፡፡ እነዚህን ከሀዲዎችና ባንዳ

ምሁራን ማጋለጥና መታገል ያስፈልጋል፡፡ ዴሞክራሲና ሕዝባዊ የሽግግር መንግስት አማራ ጭ በቅድሚያ የኢትዮጵያና ኢትዮጵያን ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት የሚያሸጋግር መሆን አለበት፡፡ ሀገራችንን የሚያፈራርስ ሽግግርን ልንደግፍ አንችልም፡፡ በዴሞክራሲ መብት ሽፋን ገንጣዮች ሀገርን የሚያፈርሱበትን ሂደት ልንደግፍ አንችልም፡፡ የኤርትራ ተመክሮ ትምህርት ለግሶናል፡፡ 20 ዓመት የወያኔ ተመክሮ ትምህርት ሰጥቶናል፡፡ ኦነግና ኦብነግም ዓላማችን ይህ ነው ብለው ሳይደብቁ ነግረውናል፡፡ ይህ የነሱ ተጨባጭ የሀገርና የሀቅ ተጨባ ጭ ነው ብለን መውሰድ የለብንም፡፡ አያሌ በወያኔም በሆድ አደሮችም የተፈጠሩ ቡድኖች አሉና እነዚህ የሀገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ ገላጭ ናቸው ብሎ ቁም ነገር መስጠቱ ስህተት ይሆናል፡፡ ዴሞክራሲ ስንል በሀገራችን የፖለቲካ ህይወትና የነገ ዕጣ ሚዛን ያላቸውን የሚመ ለከት እንጂ የጠዋት ጤዛዎችን በሚዛን የሚያስገባ ሊሆን አይገባውም፡፡

ዴሞክራሲ ስንል ለሕዝብ ገደብ የለሽ መሆኑን ስናምን ግና ሀገርን ለመገነጣጠል ለተነሱት ገደብ አልባ የሚሆን አይደለም፡፡ በህዝብ ውሳኔ ሽፋን ሀገርን ሊገነጣጥሉ መብት የሚሰጥ ዴሞክራሲ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ ዴሞክራሲ አይደለምና ፡፡ ይህን መረዳት አስፈላጊ ነው፡፡ የሀገር ህልወና ከሁሉም በፊትና በላይ የሚቀመጥ ነው፡፡ሀገርን የሚሰርዝ ዴሞክራሲ ባዳ ነው፡፡ ለዚህም ነው ዛሬ የታፈነ የተረገጠ ሕዝብ በነፃ ደምፁን ማስማት ይሳነዋል የምንለ ው፡፡ ሕዝበ ወሳኔ በቅድሚያ የሕዝብን ነፃነት ጠያቂ ነው፡፡ በነፃነትና ባርነት፤ በአረመኔነትና አመራጩ መሀል ከሆነ ምርጫወ ሕዝብ የተሻለ የተባለውን መምረጡ አይቀሬ ነው፡፡ ማንም ባርነትንና ጭቆናን አይመርጥምና፡፡ ዋናውን የመገንጠል ወይም የመገነጣጠል ዓላማ ግን ሽፋ ፍኖ፤ ዴሞክራሲን ሽፋን ካባ በማድረግ ግንጠላን አመቻቹ ሊሚሉት መሳሪያ ሊሆን አይገባ ም.፡፡ ዴሞክራሲና ግንጠላ ለየቅል ናቸው፡፡ በዴሞክራሲ ሽፋንም የሀገርን ህልወና ለማጥፋ ት መነሳቱ ውግዘትን የሚያስከትል የክህደት ስምሪት ነው፡፡
ከሀዲ ከመባል ያድነን!